ሚያዝያ 9 2001 ዓ.ም

# ከዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉአላዊነት የተሰጠ መግለጫ

## ትንኮሳና ወከባ ይቁም !

ኢህአዴግ መጪው ምርጫ ነፃ፣ ፍትሓዊና ዴሞክራሲያዊ እንደሚሆን በተደጋጋሚ በመገለጽ ላይ ይገኛል። አልፎ አልፎም ምርጫው ሰላማዊ እንደሚሆን ይናገራል። ሆኖም በተግባር እየሆነ ያለው ከዚህ ፍፁም የተለየ ነው። በአገሪቱ ባሉት ሐቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ከፍተኛ ትንኮሳዎችና ወከባዎች እየተጧጧፉ ይገኛሉ። በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች በአባሎቻቸው ላይ እየተፈፀሙ ያሉትን የሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች ጥሰቶች እያሰተጋቡ ቢሆንም ገዥው ፓርቲ ግን ይህን ስሞታቸውን መሠረት የሌለውና የፈጠራ ወሬ ነው በማለት ያጣጥለዋል። ይህ የኢህአዴግ ማጣጣል በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት ቃለ ምልልስም በአፅኖት ተስተጋብቷል። ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉአላዊነት ኢህአዴግ በአባሎቹና በአመራሩ ላይ እያደረሰ ያለውን ተደጋጋሚና ቀጣይ ትንኮሳዎችና ወከባዎች ምናልባት በሂዴት ያርማል በሚል ተስፋ ሳይገልጸው ቆይቷል። መሻሻሉ ቀርቶ ሁኔታው ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ በመሄዱ የሚደርስበትን እያንዳነዱ ወከባና ማስፈራርያ ለህዝቡ ለመገለፅ ተገዷል።

ዓረና በቅርቡ ብሽሬ እንዳ ሥላሴና በተምቤን ዓቢ ዓዲ ከተሞች ጽሕፈት ቤቶችን መክፈቱ ለሕዝቡ ታላቅ ዜና ሆኗል። እነዚህ ሁለት አካባቢዎች ደርግን ለመጣል በተደረገው ትግል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ ናቸው። በተለይ ሽሬ ህወሓት የትጥቅ ትግል የጀመረበት አካባቢም ነው። እነዚህ ሁለት አካባቢዎች በጠንካራ ፀረ ደረግ ትግላቸው ብቻ ሳይሆን የህወሓትን ኢፍትሓዊ አስተዳደር በመቃወምም ይታወቃሉ። የተምቤን ዓቢዪ ዓዲ ህዝብ ያለውን የህወሓት ከባድ አስተዳደራዊ ጫና ሳይበግረው በርካታ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን በማንሣት በአደባባይ ሠልፍ እንደወጣ የቅርብ ታሪኩ ይመሰክራል። ይህ ተቃውሞው ህወሓት በወሰደው የአካባቢውን ምክር ቤት ማፍረስና በነዋሪዎች ላይ በደረሰው ከፍተኛ ወከባ ተቋጭቷል። የዚህ ዓይነቱ ችግር ቢያጋጥመውም የተምቤን ህዝብ ችግሮችን በመቋቋም የህወሓትን ብልሹ አስተዳደር በመቃወም ላይ ይገኛል። ሽሬም የህወሓትን ኢፍትሓዊ አገዛዝ በመቃወም የታወቀ ሕዝብ ነው። ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ሉአላዊ ግዛታችን የሆነውን ባድመንና አካባቢውን ለሻዕብያ አሳልፎ ለመስጠት የወሰነውን ውሳኔ በጥብቅ በመቃወም ውሳኔው ተግባራዊ እንዳይሆን በጥብቅ ከተቀወሙት አካባቢዎች አንዱ ነው። ከዚህ ሌላም በአካባቢው ህወሓት የሚደርስበትን በደልና መጥፎ አስተዳደር በመቃወም ይታወቃል። እነዚህ ሁለት አካባቢዎች ይህን መሰሉ ተቃውሞ በማሰማታቸው ለተቃዋሚዎች ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ተገምተው በጥረጣሬ ሲታዩ ቆይተዋል። እንዲያውም ዓረና ከመመሥረቱ አስቀድሞም ቢሆን የተቃዋሚ ደጋፊዎች በመባል በህወሓት ጎራ ስማቸው ሲነሳ ቆይቷል።

በነዚህ አካባቢዎቸ የከፋው የህወሓት ወከባና ጫና እየታየ ያለው ግን ዓረና ከተመሠረተና በነዚህ አካባቢዎች እንቅስቀሴ ከጀመረና ጽሕፈት ቤቶች ከከፈተ በኋላ ነው። በአጭር ጊዜ ውሰጥ ወከባዎችና ትነኮሳዎች ተበራክተዋል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነውም በቅርቡ በሽሬ እንዳሥላሴ የዓረና ጽህፈት ቤት ከተከፈተ በኋላ እየተካሄዱ ያሉትን ጫናዎችና ወከባዎች መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።

1. የሽሬ ጽህፈት ቤት በተከፈተ ማግሥት የመንግሥት ሠራተኞቸ ስብሰባ ተጠርቶ በዓረና ላይ ከፍተኛ የጥላቻ ቅስቀሳ ተካሂዷል። የህወሓት መፈጠሪያ በሆነችው ሽሬ አማረኛ ተናገሪ ቅንጅቶች ጽህፈት ቤት መክፈታቸው ለአካባቢው እንደውርደት እንደሚቆጠር ቅስቀሳ ተደርጓል።

በኛ በኩል ይህ ቅስቀሳ ህዝቡ በጽህፈት ቤቱና በዓረና ላይ ጥቃት እንዲፈጽም የሚገፋፋ ቅስቀሳ እንደሆነ ተመልክተነዋል ። የህወሓት ካድሬዎች ይህን ይበሉ እንጂ አንዳንድ የመንግሥት ሠራተኞች ዓረና በጠላትነት የሚታይ ከሆነ ለምን ፍቃድ ተሰጠው? ህዝቡስ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን የመማዛዘን ብቃት የለውምን? የሚሉ ጥያቄዎችን አቅርበዋል። በቅን ልቦናቸው ይህን የተናገሩትን ደግሞ የዓረና ወኪሎች ተብለው በጥርጣሬ እንዲታዩ ተደርገዋል። ሰማቸውን ለመገለጽ ያልፈለጉ የስብሰባው ተሳታፊዎች ወካባና ትንኮሳ እየደረሰባቸው መሆኑን ለድርጅታችን አስታውቀዋል።

2. ባለፈ ሳምንት የመሰሪያ ቤታችን ቁልፍ ተሰብሮ ተገኝታል። ይህም ሰብሮ ለመግባት የተደረገ ሙከራ መሆኑን ተገንዝበናል። ከዚህ ሌላም በመስሪያ ቤቱ አካባቢ የተለጠፉት ድርጅቱን የሚያስተዋውቁ ጽሑፎች ተቀዳድደዋል። መንግሥት መስሪያ ቤተችንና አባሎቻችንን ከጥቃት የመከላለከል ግዴታ ቢኖርበትም በበኩላችን የተገነዘብነው ግን የዚህ ተፃራሪ ነው።

3. ለዓረና ቤት ያከራየው ሰውም ውሉን እንዲሰርዝ ግፊት እየተደረገበት እደሚገኝ አውቀናል። ቤቱን የተከራየነው ረዘም ላለ ጊዜ ቢሆንም እኛን ለማሰለቀቅ ሲባል በባለቤቱ ላይ ከፍተኛ ግፊት እየተደረገ መሆኑን ተገንዝበናል።

4. መስሪያ ቤቱን በፈቃደኛነት በማገልገል ላይ ባለው አባላችንም ከፍተኛ የማባበልና የማስፈራርያ ተግባር እየተካሄደበት ነው። ዓረናን ማገልገሉ ከተወ ቋሚ ሥራና ዳጎስ ያለ ደመወዝ እንደሚሰጠው ማባባያ እየቀረበለት ይገኛል። ቤተሰቦቹም ከፍተኛ ጫና ስለደረሰባቸው የሚሰጠውን አገልግሎት እንዲያቋርጥ ግፊት እያደረጉ ይገኛሉ።

5...በከተማው ተከታታይ ስብሰባዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ። በነዚህ ስበሰባዎች እየቀረቡ ያሉት ቅስቀሳዎች እጅግ አፋኝና ሕገ መንግሥቱን የሚጻረሩ ናቸው። የዓረናን አመራር አባላት በግል እየጠቀሱና ፓርቲውን እያነሡ ጸረ ሰላም፣ ጸረ ልማትና ጸረ ትግራይ መሆናቸውን ለማስረገጥ እየሞከሩ ይገኛሉ።

እንግዲሀ በሽሬ እንዳሥላሴ በድርጅታችን ላይ እየተፈጸሙ ያሉት ወከባዎችና ትንኮሳዎች ከብዙ በጥቂቱ ከላይ የተገለጹት ናቸው። በድርጅታቸን ላይ ተመሳሳይ ስም የማጥፋትና የወካባ ዘመቻዎች በሌሎች አካባቢዎችም በስፋት እየተካሄዱ ይገኛሉ። በወካባው የተደናገጠ የመቀሌው ቤት አከራያችንም ቤቱን እንደንለቅ ጠይቆናል። የዓቢዩ ዓዲ ጽሕፈት ቤት ለመከራየት ባደረግነው ሙከራም ሦስት አከራዮች ከተሰማሙ በኋላ በድርጅቱ በደረሰባቸው ጫና ምክንያት ቃላቸውን አጥፈዋል። በድርጅታችን ላይ እየተደረገ ያለው ትንኮሳና ወከባ ማለቅያ የለውም።

ገዥው ፓርቲ ስለ ፖለቲካ ምኅዳሩ ሰፊ እንደሆነና መጪው ምርጫም ነጻና ፍትሓዊ እንደሚሆን ቢደሰኩርም በተጨባጭ መሬት ላይ ያለው ሁኔታ ግን ፍጹም የተለየ ነው። እጅግ የተደናገጡት ገዥ ፓርቲና ካድሬዎቹ ለሚቀጥለው ትውልድ በሥልጣን ለመቆየት ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉትንና የሌላው ዓለም መሠረታዊ መስፈርት የሆኑትን ዴሞሞክራሲያዊ መብቶች ለመርገጥ ቆርጠው ተነስተዋል። ከዚህ ሌላም የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመርገጥ በሥልጣን ለመቆየት ወስነዋል። ሂዴቱ እንዴት እንደሚቋጭ በጉጉት የምንጠብቀው ነው።